# ደምብ-ሥርዓት

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

ተዛማጅ ደምቦችና መመሪያዎች፡- ACA, ACF-RA, ACH, ACH-RA, COA, COA-RA, COC-RA, COE-RA, COF-RA, COG-RA, EBA-RA, EBJ-RA, EBK-RA, ECC-RA, EEA-RA, EKA-RA, GKA-RA, IGN, IGO-RA, JGA-RA, JGB-RA, JHC, JHC-RA, JHF-RA, JHG-RA, JPD, JPD-RB, በድርድር የተከናወኑ የማሻሻያ ስምምነቶች

ሃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡- Chief of Teaching, Learning, and Schools; Chief of Strategic Initiatives; Chief of Staff Montgomery County Public Schools

## ክስተት ሪፖርት ማድረግ

I. **ዓላማ**

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የማስተማሪያ፣ የመማሪያ እና ትምህርት ቤቶች (OTLS)፣ የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ማሻሻያ ጽሕፈት ቤት (OSSI)፣ የሥርዓት-አቀፍ ደህንነት እና ድንገተኛ ሁኔታ ማኔጅመንት (DSSEM) ሌሎች የ MCPS ጽ/ቤቶች፣የሕግ አስከባሪዎች እና ሌሎች የውጭ ኤጀንሲዎች ጤናን፣ ደህንነትን እና የደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ስለማድረግ መመሪያን ለመስጠት።

በክስተት ማኔጅመንት ሲስተም (IMS) ወይም በሌሎች የታወቁ የሪፖርት ፕሮቶኮሎች አማካኝነት የስርዓት አቀፍ ምላሾችን ለማስተባበር እና በአግባቡ ለመምራት

እንደአስፈላጊነቱ እነዚህን ክስተቶች ለህዝብ ሪፖርት ስለማድረግ መመሪያ ለመስጠት

II. **ትርጓሜዎች**

A. የ MCPS ንብረት ማለት በ MCPS ይዞታነት ያሉ ወይም የሚሠራባቸው ማናቸውም ት/ቤት ወይም ሌላ መገልገያና ተቋም፣ የ MCPS አውቶቡሶች፣ ሌሎች የMCPS ተሽከርካሪዎች፣ እና/ወይም ተማሪዎች የሚገለገሉባቸው ማናቸውም የMCPS እንቅስቃሴዎች የሚካሄድባቸው መሬቶች ማለት ነዉ።

B. ርዕሰመምህር(ት)/ዳይሬክተር ማለት ለአንድ ትምህርት ቤት ወይም ጽ/ቤት ኃላፊነት ያለው/ያላት አስተዳዳሪ ወይም የእነርሱ ተወካይ ማለት ነው።

C. A ሪፖርት መደረግ የሚገባው ክስተትማለት ማንኛውም – ክስተት ነው

1. በ MCPS ንብረት ላይ ወይም ትም/ቤት ስፖንሰር ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ጋር ታያያዥ ሆነው የተከሰቱ ለ MCPS ሰራተኞች ሪፖርት የተደረጉ፣ እና

2. ለሰራተኞች ወይም ተማሪዎች በተወሰነ ደረጃ ስጋት፣ ጉዳት፣ ወይም ጉዳት ለማድረስ ማስፈራራት፣ የትምህርት ቤት ስራዎችን በከፍተኛ ሁኔታ ማሰናከልን ያካትታል፣ ወይም

3. ሰራተኞችን ወይም ተማሪዎችን ስጋት ላይ የሚጥል እና ወደ ማህበረሰብ ስጋት ወይም ከፍ ያለ የፖሊስ ወይም የሕግ ጉዳይ ሊሆን ይችላል።

**III. ለክስተቶች የምላሽ አሰጣጥ አፈጻጸሞች**

A. አስቸኳይ የአደጋ ክስተት ምላሽ

ከትምህርት ቀን በፊት ወይም በኋላ የሚፈጸሙትን ጨምሮ፣ ሪፖርት መደረግ ያለባቸው የሚከሰቱ ክስተቶችን፣ በት/ቤት፣ በሥራ ቦታ ላይ ያሉ ሰራተኞች አስቸኳይ ሁኔታውን በወቅቱ በትምህርት ቤት/በሥራ ጣቢያ ላይ የተፈጠረ የቀውስ እርምጃ እቅድን መሰረት በማድረግ፣ ሁኔታውን እንደሚከተለው ሪፖርት ያደርጋሉ፦

1. ትምህርት ቤት/ጣቢያ ላይ የሚገኙ ሰራተኞች ለርእሰመምህር/ዳይሬክተር ወዲያውኑ ያሳውቃሉ

2. ርእሰ መምህር/ዳይሪክተር ወይም ተወካይ ለህግ አስከባሪዎች ወዲያውኑ (ከታች በክፍል III.B እንደተገለፀው ዓይነት ክስተት ከተፈፀመ) ያሳውቃል/ታሳውቃለች

3. ርእሰመምህር/ዳይሬክተር ወይም ተወካይ ከ OSSI ጋር ወዲያውኑ ወይም ድንገተኛ ሁኔታው እንደጠየቀ በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ ግንኙነት ያደርጋል/ታደርጋለች

    a) ትምህርት ቤቱ/በጣቢያ የሚገኘው የቀውስ እርምጃ እቅድ ላይ OSSI ጋር ለመገናኘት ኃላፊነት ያለበትን ሰራተኛ መመደብ አለበት።

    b) OSSI እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች የ MCPS ቢሮዎችን ያሳውቃል (ከዚህ በታች ክፍል IV ይመልከቱ።

4. ከትምህርት ሰዓት በፊት ወይም በኋላ አንድ ሁኔታ ከተከሰተ (ለምሳሌ፦ በሳምንቱ መጨረሻ የትምህርት ቤት መቋረጥ ወይም ንብረት የማውደም ወንጀል) እና ለስርዓት አቀፍ ደህንነት እና የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር መምሪያ (DSSEM) እና/ወይም ለርዕሰ መምህር ሪፖርት ከተደረገ፣ ሁለቱም የ DSSEM ሰራተኞች እና ርዕሰ መምህሩ OSSI በአስቸኳይ ማነጋገር አለባቸው።

5. ድንገተኛ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በክስተቱ ላይ ቀጥታ ተሳታፊ ለሆነ/ች/ኑ ተማሪ ወላጆች/አሳዳጊዎች እንደሁኔታው ወዲያውኑ ማሳወቅ -

    a) ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ እና ለሠፊዉ ህብረተሰብ ማሳወቅን በተመለከተ ከዚህ በታች ክፍል Vን ይመልከቱ።

    b) በ MCPS ደንብ JHC-RA ላይ እንደተቀመጠዉ፣ የልጅ መጎሳቆል እና ቸልተኝነት ጥቃትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ፣ የተጠረጠሩት የልጅ መጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ሁኔታዎችን ለወላጆች/ሞግዚቶች በማን አማካይነት ማሳወቅ እንደሚገባ ለመወሰን ርዕሰመምህራን/ተወካዮች ከህግ አስከባሪዎች ጋር መተባበር ያስፈልጋል።

b) አፍራሽ/አጥፊ መሣሪያዎችን ማምረት ወይም ይዞ መገኘት (ፈንጂ፣ የሚያቀጣጥል፣ ወይም መርዛማ ቁሶችን ከሚያፈነዱ ነገሮች/መሣሪያዎች ጋር ተዋህዶ ወይም ይህን ለመከወን የተሻሻሉ) (እንዲሁም MCPS ደንብ EKA-RA ይመልከቱ፣ድንገተኛ ሁኔታ እና የአደጋ ዝግጁነት

c) ስለቦታው ወይም የሚጎዳ መሣሪያ መፈንዳትን እያወቁ/ሆን ተብሎ የሀሰት ሪፖርቶችን ማቅረብ

d) ቁጥጥር የተደረገበት አደገኛ እፅ ማሰራጨት ወይም ማምረት

e) ከትምህርት ቤቱ የጤና ክፍል ውጭ የሕክምና ክትትል የሚያስፈልገው በሌላው ላይ አካላዊ ጥቃት በሚመለከት 911 ጥሪ ሲደረግ (የተጠረጠረ የሕፃናት በደል እና/ወይም ቸልተኝነት፣ እንዲሁም የ MCPS ደንብ JHC-RA፣የሕፃናት በደል ሪፖርት ማድረግ እና ቸልተኝነትን መመርመር)

f) ስርቆት (የተሰረቀው ንብረት ዋጋ $ 500 ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ በአንድ ተመሳሳይ ወንጀለኛ የተፈጸመ የአንድ ጊዜ ክስተት ወይም ተከታታይ ክስተቶች)

g) አውቆ እያወዛወዙ ለማስፈራራት ወይም ጉዳት ለማድረስ ጥቅም ላይ ያልዋለ በትምህርት ቤት ንብረት ላይ አደገኛ ወይም ገዳይ መሣሪያ ይዞ መገኘት [2]

h) የተከለከለ ወይም ቁጥጥር የሚደረግበት አደገኛ እፅ መጠቀምን ወይም ሆን ተብሎ ለማሠራጨት ይዞ መገኘት (የቦርድ ፖሊሲ IGN ይመልከቱ፡- "በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌላ የአደንዛዥ እፅ መድኃኒት መጥፎ አጠቃቀምን መከላከል፣ እና MCPS ደንብ IGO-RA፣ "ተማሪዎች የተሳተፉበት የአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና የሌሎች እጾች መጥፎ አጠቃቀም ክስተት የመቆጣጠር መመሪያ)።

(1) በምርመራ ወቅት የሕግ አስከባሪዎች ቀዳሚነቱን ቢወስዱም/ባይወስዱም፣ የ MCPS ሰራተኞች ቁጥጥር የሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች እንደሆኑ የሚጠረጥሩትን ነገር ወደ እነርሱ ሲመጣ አግባብ ወዳለው የሕግ አስከባሪ ድርጅት መምራት አለባቸው።

(2) ነገር ግን፤ ከተማሪው(ዋ) ላይ ማቴሪያሉ የተገኘው ስለመዳኒት አጠቃቀም የምክር አገልግሎት በሚሰጥበት ኮንፈረንስ ወይም ኢንፎርሜሽን በሚጠየቅበት/በምትጠየቅበት ወቅት ከሆነ፣ የ MCPS ሠራተኛ ስለተማሪው(ዋ) ማንነት በሚስጥር መጠበቅ እንዳለበ(ባ)ት የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል (MCPS ደንብ IGO-RA የመልከቱ፡- "ተማሪዎች የተሳተፉበት የአልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች የአደንዛዥ እጽ መድሃኒቶች መጥፎ አጠቃቀም የመቆጣጠር መመሪያ)።

C. በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረቱ ዝግጅቶችን በሚይዙበት ጊዜ በጣም ጥሩውን የድርጊት አካሄድ ለመወሰን የቀሩ አስፈላጊ ሁኔታዎች፣ ሕግ እና MCPS ይተባበራሉ፤ በት/ቤት ውስጥ አብዛኛዎቹ

---

[2] □□□ □□□ □□□□□ □□□ □□□□□ □□□ □□□ □□□□□ □□□□□□□ In re Melanie H.□ 120 Md.App.158 (1999) □□□□□□-

ክስተቶች አሁን ያሉትን ጠቅለል ያሉ የትምህርት ቤት ሀብቶችን ለመጠቀም ማስተዳደር ይችላሉ።በ MOU- CEO ያልተሸፈኑ ክስተቶችን፣ ትምህርት ቤቱ ለፖሊስ ሪፖርት ከማድረጉ በፊት፣አግባብነት ያለውን የአሰራር ሒደቶችን ተግባራዊ እንዲያደርግ ይጠበቃል።

D. ምንም እንኳን ስለደረሰው ክስተት ሁሉም ነገር ተሟልቶ ባይጠናቀርም የሚከተሉት ክስተቶች በ1 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለ OSSI ሪፖርት መደረግ አለባቸው። እንደዚህ አይነት ክስተቶች እንደአስፈላጊነቱ ለህግ አስፈፃሚዎች ወይም ለሌሎች ኤጀንሲዎች አንድ በአንድ/እንደ እያንዳንዱ ጉዳይ መሰረት ተጨማሪ ሪፖርት ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡-

1. ሌሎች የሠላም/የደህንነት ክስተቶች

   a) ማንኛውም ስለ እሳት አደጋ ለመታደግ የሚቀርብ ጥያቄ

   b) እሳት (በተጨማሪም የ MCPS ደንብ EBA-RA፣ከእሳት አደጋ መጠበቅ) ይመልከቱ፡-

   c) በ MCPS ንብረቶች ላይ ማንኛውም ዓይነት አካላዊ ወይም በወረቀት መታሰር

   d) ተማሪን መፈተሽ እና/ወይም የተማሪ ንብረት መያዝ (በተጨማሪም MCPS ደንብ JGB-RA፣ስለ ፍተሻና መውረስ ይመልከቱ፡-

   e) ዘግቶ መቆየት፣ ለቆ መውጣት ወይም ከለላ ማግኘት (በተጨማሪም MCPS ደንብ EKA-RA፣የአስቸኳይ ጊዜ እና የአደጋ መከላከል ዝግጁነት ይመልከቱ)

   f) የአደገኛ ቁሳቁሶች ክስተት (በተጨማሪም የ MCPS ደንብ EKA-RA፣ የአስቸኳይ ጊዜ እና የአደጋ መከላከል ዝግጁነት) ይመልከቱ፡-

2. አስቸኳይ/ድንገተኛ የጤና እንክብካቤ

   a) ለድንገተኛ ጊዜ የሕክምና እርዳታ ማንኛውም ጥያቄ (በተጨማሪ የ MCPS ደንብ EBJ-RA፣ድንገተኛ እንክብካቤ እና የመጀመሪያ እርዳታ በትምህርት ቤቶች ውስጥ) ይመልከቱ፡-

   b) ከባድ የአካል ጉዳት የሚያደርስ አይነት ክስተት፣ ለሞት የሚዳርግ፣ አካለ ጎደሎነትን የሚስከትል ወይም በቋሚነት አካለስንኩልነት የሚያስከትል ተደርጎ የተገለጸ ማናቸውም አይነት ጉዳት

   c) ማንኛውም የድንገተኛ ጊዜ የጤና እንክብካቤ ሁኔታ የስቴት ወይም የፌዴራል ሪፖርት መስፈርቶችን በመከተል (ለምሳሌ፡- ከአናፍላሲሲስ ጋር የተዛመደ የኢፒነፍሪን አሰጣጥ፣ ከመጠን በላይ የተወሰደ ኦፒዮይድ ጋር የተዛመደ ናሎክሲን አሰጣጥ፣ በሽታ አምጪ ተውሳኮች መከሰት፣ ወይም ውጫዊ አውቶማቲክ ዲፊብሪላተር አጠቃቀምን) (እንዲሁም የ MCPS ደንብ JPD-RB ይመልከቱ።አናፍላሲስ ለሚያጣድፋቸው ተማሪዎች የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ፣ እና የቦርድ ፖሊሲ IGN፣በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ አልኮል፣ ትምባሆ እና ሌሎች የአደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ መጠቀምን መከላከል)

   d) የተረጋገጡ ተላላፊ በሽታዎች (ለምሳሌ፡- Pertussis ወይም Tuberculosis)

e) በ MCPS ደንብ EBH-RA፣ተማሪ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ሪፖርት ከማድረግ ጋር የሚያያዙ ሌሎች አጋጣሚዎች፡-

(1) ማንኛውም በጭንቅላት/ራስ፣ ዐይን፣ አንገት፣ ወይም አከርካሪ ላይ የሚደርስ ጉዳት፣

(2) እብጠት የሚያስከትል ማንኛውም የአጥንት ወይም የመገጣጠሚያ ጉዳት፣

(3) ቀዳዳ ያለው ቁስል፣ ቃጠሎ፣ ወይም መሠፋት የሚያስፈልገው መቆራረጥ/ቁስል፣

(4) ማንኛውንም መድሃኒት፣ ኬሚካል፣ ወይም ባዕድ ነገሮችን መዋጥ፣ ማንኛውንም የተከለከለ እፅን መዋጥ/መጠቀም፣ ወይም

(5) ማንኛውም የእንስሳት ንክሻ (በተጨማሪ የ MCPS ደንብ EBK-RA፣ስለ እንስሳት ንክሻ ሪፖርት ማድረግ እና እንክብካቤ) ይመልከቱ።

3. የንብረት መጎዳት/ብልሽት

a) አስፈላጊ መሣሪያዎች፣ መገልገያዎች፣ እና/ወይም አገልግሎቶች በከባድ ሁኔታ የማይሠሩ

b) የትምህርት ቀንን በሚያደናቅፍ ደረጃ የተፈጸመ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት በተጨማሪ (MCPS ደንብ ECC-RA ይመልከቱ) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በንብረት ላይ የደረሰ ጥፋት ወይም ጉዳት)

4. ዲሲፕሊን

የታቀደን የትምህርት ቀን ለማደናቀፍ ሊደርስ የሚችል ወይም ትክክለኛ ከባድ የሁከት ስነ ምግባር

IV. **ክስተቶችን የመቆጣጠር/የማስተዳደር ስልት (IMS) እና ሌሎች ሪፖርት ማድረጊያ/የሪፖርት አደራረግ ፕሮቶኮሎች/ሥርአቶች**

A. ከተወሰነ ልዩ ሁኔታዎች ጋር፣ በትምህርት ቀን ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሶር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚከሰቱ ሁነቶች/ክስተቶች ለ OSSI ሪፖርት ይደረጋሉ እና እንደአስፈላጊነቱ በ IMS አማካይነት የክስተት አስተዳደር የተቀናጀ "አንዴ መቆም"/one-stop አቀራረብ ለማስተዋወቅ ይሰራጫሉ።

1. ከርእሰመምህር/ዳይሬክተር/ተወካይ ጥሪ ሲደርሰው፤ OSSI በ IMS ሪፖርት ያዘጋጃል እና IMS በመጠቀም ሌሎች ቢሮዎችን ለማነጋገር፣ በአግባብ ለመምራት እና ከሲስተሙ የሚሰጡ ምላሾን ለማስተባበር ከሚመለከታቸው ቢሮዎች ጋር ለመገናኘት፣ በዚህ የሚገደብ ሳይሆን፡- Risk Management, Department of Communications, DSSEM, Student and Family Support and Engagement, Student Welfare and Compliance, Office of the General Counsel (OGC), and Employee Engagement, Compliance, and Investigations (EECI) የመሳሰሉትን ክፍሎች በማስተባበር ምላሽ ይሰጣል።

2. ርእሰመምህር/ዳይሬክተሩ/ሯ /ተወካይ ክስተቱን በተመለከተ በ 48 ሰዓታት ውስጥ በተጨማሪ

መረጃ የ IMSን ዘገባ ያሻሽሉና ሁሉም አስፈላጊ መረጃዎች በሚቀርቡበት ጊዜ የክስተቱ ሪፖርት እንዲዘጋ ያደርጋሉ።

B. የሚከተሉት ክስተቶች በስቴት ወይም በፌዴራል መስፈርቶች፣ በ MOU-CEO እና/ወይም በሌሎች የ MCPS ደንቦች ላይ በተዘረዘሩት መሠረት ስለ ሪፖርት አቀራርብና ምላሽ የመስጠት መስፈርቶች ተገዢ ናቸው፣ አንዳንዶቹ ከ OSSI በተጨማሪ፣ ለ MCPS ጽ/ቤቶችም ሪፖርት ማድረግ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

1. የልጅ መጎሳቆል እና/ወይም ችላ መባል ሪፖርት መደረግ ያለበት፦ በ MCPS ደንብ JHC-RA ድንጋጌ መሠረትየልጅ ማጎሣቆልን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ ማካሄድ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎቶች እና/ወይም ለጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎቶች ሪፖርት ይደረጋል።

2. የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች የአውቶቡስ አደጋዎችን በቀጥታ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የመጓጓዣ ዲፓርትመንት/MCPS Department of Transportation (DOT) ሪፖርት ያደርጋሉ። የአደጋ ስፍራ/ቦታ ኃላፊነት፣ ማሳወቅ፣ እና የሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች ከስቴትና ከፌዴራል መስፈርቶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው እና በ MCPS ደንብ EEA-RA፣ ስለ ተማሪ ትራንስፖርት የሚለው ላይ የተዘረዘሩ ናቸው። የአውቶቡስ አደጋ ወይም ሌላ የአውቶቡስ ዉስጥ ክስተት ምክንያት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር መገናኘት ሲያስፈልግ፣ ትምህርት ቤቱ ስለተፈጠረው ክስተት ከ DOT ከሰማ በኋላ ወዲያውኑ ለ OSSI መደወል አለበት።

3. አንድ የሥራ ባልደረባ በተማሪ ላይ ስለሚፈጸም ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ፣ እና ወካባ፣ በተማሪ ላይ የተፈጸመ ጾታዊ ጥቃት ጭምር ሪፖርት እንዳገኘ(ች) መረጃው/ኢንፎርሜሽኑ ወዲያዉኑ በ MCPS ቅጽ 230-35 ተቀናብሮ ለርእሰመምህር/ተወካይ ሪፖርት መደረግ አለበትስለ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም የማስፈራሪያ ሪፖርት ቅጽእና እንደሚከተለው ምርመራ ይካሄዳል፦

   a) ከጾታዊ ጥቃት ሌላ፣ በተማሪዎች ላይ ጉልበተኝነት/ወከባ/ማስፈራራት በ MCPS Regulation JHF-RA በተደነገገው መሠረት በዶኩመንት ተይዞ በርእሰመምህር(ት) አማካይነት ምርመራ ይደረጋል በተማሪዎች ላይ የሚፈጸም ጉልበተኝነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት።

      (1) ክስተቱ የተመዘገበው በሲነርጂ ነው።

      (2) ክስተቱ በ ሰክሽንስ III.B እና/ወይም III.C. ላይ የተገለጸውን መስፈርት የማያሟላ ከሆነ ወደ OSSI መደወል ወይም IMS ላይ ሪኮርድ ማድረግ አስፈላጊ አይሆንም። ትምህርት ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ አግባብ ያለው መመሪያ ለማግኘት OSSI ን እንዲያነጋግሩ ይመከራል።

   b) በተማሪ ላይ የሚፈጸም ጾታዊ ጥቃት በ MCPS ደንብ ACF-RA ላይ በተደነገገው መሠረት ሪፖርት መደረግ እና ምርመራ መደረግ ይኖርበታል፣ጾታዊ ጥቃት። አንዳንድ የወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነቶች የወንጀል ቅጣቶችን ወይም የሕፃናት ጥቃትን የሚያስከትል የወንጀል ድርጊት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ስለሆነም በሕግ አስከባሪዎች ምርመራ ወይም በ MCPS ደንብ JHC-RA፣ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ማድረግ እና መመርመር፣ እና/ወይም የ MOU-CEO ድንጋጌዎች።

      (1) ማናቸውም የተወሰነዉ ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች ከተጠናቀቀ በኋላ፣

ርእሰመምህር/ተወካይ OSSI መደወል አለበ(ባ)ት፣ እና ጥሪውም እንደአግባብነቱ በ IMS አማካይነት ሠነድ ተደርጎ ለአስፈጻሚ ክፍል ይሠራጫል። ከ OSSI ጋር በመተባበር፣ ስለተማሪ ጾታዊ ጥቃት ሪፖርት ስለተደረገው ክስተት በ MCPS ስለተወሰደው እርምጃ አስፈጻሚው ክፍል የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት።

(2) የሕግ አስከባሪ አካላት ከተሳተፉ፣ የ MCPS ምላሽን ከህግ አስከባሪዎች ጋር ለማስተባበር የተማሪ ደህንነት ጥበቃ እና ስነ ስርአት ማስከበር ክፍልን ማማከር አለበት። የተማሪዎች ደህንነት እና ስነ ስርአት አስከባሪ ከሕግ አስከባሪዎች ጋር ተገቢውን ቅንጅት ለማረጋገጥ ለ DSSEM ያሳውቃል።

(3) በ MCPS ደንብ ACF-RA፣ ስለ ወሲባዊ ትንኮሳ ላይ እንደተገለጸው የተቀናበረ ሪኮርድ ክስተት በርእሰመምህር/በተወካይ ይመዘገባል።

4. ማንኛውም የመገደብ ወይም የማግለል ሁኔታዎች (የ MCPS ደንብ JGA-RA፣ የመማሪያ ክፍል አመራር እና የተማሪዎች የባህሪ ጣልቃ ገብነቶችን ይመልከቱ) ለልዩ ትምህርት ጽ/ቤት ሪፖርት ተደርገው በ Synergy ይመዘገባሉ። ለወላጅ/አሳዳጊ በ 24 ሰዓት ውስጥ ማሳወቅ ያስፈልጋል። በተጨማሪ በትምህርት ቀን መጨረሻ ወላጅ/አሳዳጊ ጋር ለመገናኘት ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት።

5. ሠራተኞች ወይም በጎፈቃደኞች ከሥራ ጋር የተያያዙ ጉዳቶች ሲደርስባቸው በቀጥታ ለ CorVel ኮርፖሬሽን ሪፖርት ይደረጋል፣ ለ MCPS የሥራ ባልደረቦች የሥራ ማካካሻ ጥያቄዎችን የሚያስተዳድር ሦስተኛ ወገን ነው።

6. በሥራ ቦታ ላይ ሠራተኞችን በጉልበተኝነት ማስፈራራት እና ሌሎች ከሠራተኛ ጋር የተገናኙ ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች MCPS ደንብ ACH-RA ላይ በተቀመጠው ድንጋጌ መሠረት ሪፖርት ይደረጋሉ የሥራ ቦታ ማስፈራራት፣ ጉልበተኝነት የ MCPS ደንብ GBA-RA እኩል የሥራ ቅጥር ዕድል፣ የ MCPS ደንብ GKA-RA አስተዳደራዊ ቅሬታ፣ ወይም በድርድር የተከናወኑ ስምምነቶች።

C. የትምህርት ቀንን ያላደናቀፉ አጠቃላይ ለሆነ በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት ክስተቶች (በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስን አይጨምርም) ወደ OSSI ሪፖርት አይደረግም፤ ነገር ግን በአምስት ቀን ውስጥ በትምህርት ቤቱ አማካይነት IMS ላይ መመዝገብ አለበት። ጥፋተኝነት በተገኘበት በአንድ ሰዓት ውስጥ ለ DSSEM እና OSSI ሪፖርት መደረግ እና በ IMS መመዝገብ አለበት።

D. በየወቅቱ በትምህርት ዓመቱ ውስጥ፣ OSSI፣ ከሌሎች ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር ሁሉም የክስተቶች ሪፖርት በትክክል የተጠናቀቀ መሆኑን ያረጋግጣል።

## V. ኮሙኒኬሽን

OSSI ከትምህርት ቤቱ እና ከሚመለከታቸው ሁሉም ጽ/ቤቶች ጋር፣ የኮሙኒኬሽን ዲፓርትመንት፣ DSSEM፣ EECI እና OGC ጨምሮ እንደአስፈላጊነቱ ከትምህርት ቤቱ እና ከማህበረሰቡ ጋር ለመገናኘት ኃላፊነት ለመስጠት እና ለመተባበር ይሠራል።

A. በተቻለ ፍጥነት፣ ርእሰ መምህር/ዳይሬክተር፣ OSSI፣ እና ተባባሪ ጽ/ቤቶች –

1. ተገቢውን የኮሙኒኬሽን መሪ መለየት (ማለትም ርእሰመምህር/ዳይሬክተር ሊሆን ይችላል)፣

2. ቁልፍ እውነታዎችን ለይተው ያረጋግጣሉ፣ እና

3. በህግ አስከባሪ አካላት ወይም በሌሎች ኤጀንሲዎች በሚደረጉ ምርመራዎች/ክትትሎች ላይ ጣልቃ እንዳይገባ፣ የጉዳዩን ሚስጥራዊነት፣ ግላዊነት፣ እና ጉዳዩ የሚመለከተውን ግለሰብ/የሚመለከታቸውን ግለሰቦች መብቶች ለመጠበቅ መከተል የሚገባውን ሂደቶች መወሰን ከሠራተኛ ማህበራት እና በመግባቢያ ሠነዶች ጋር የተደረጉ ስምምነቶችን መከተልን ጨምሮ።

B. የሕግ አስከባሪ አካላት በአንድ ክስተት ውስጥ ሲሳተፉ፣ መረጃው የሚለቀቀው እንደአስፈላጊነቱ ከ EECI እና OGC ጋር በመተባበር ከ OSSI ሲፀድቅ ብቻ ነው። ከልጆች በደል እና/ወይም ቸልተኝነት ጋር የተዛመዱ ክስተቶችን የሚመለከቱ ግንኙነቶች በ MCPS ደንብ JHC-RA፣ የሕፃናት በደል እና ችላ ማለትን ሪፖርት ማድረግ እና መመርመር ፣ እና የ MOU-CEO መሆን አለባቸው።

C. እንደአስፈላጊነቱ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች፣ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎች እና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት መረጃን ከመስጠትዎ በፊት ከኮሙኒኬሽን ኃላፊ ጋር የሚደረግ ምክክር ያስፈልጋል።

D. አንድ ክስተትን በተመለከተ የሚደረግ የመረጃ ልውውጥ የሚከተሉትን ነገሮች ሊያካትት ይችላል፦

1. ስለተፈጠረው ክስተት እና ችግሩን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች ዝርዝር

2. ወላጆች/አሳዳጊዎች እና/ወይም የቅርብ ተቆጣጣሪዎች ወይም ሌሎች ሊሰጡ የሚችሉት የድጋፍ ተግባራት/እንቅስቃሴዎች መግለጫ (እንደአስፈላጊነቱ)

E. ከማህበረሰብ ጋር የሚደረጉ ማናቸውም ግንኙነቶች ቅጂ ከ OSSI ጋር በፋይል ይቀመጣል እና በ IMS ማስታወሻ ይደረጋል።

**የዚህ ደንብ ታሪክ፦ የቀድሞ ደንብ ቁ.** 285-9፣ ኅዳር 19 ቀን 1976 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ጃኑወሪ 31 ቀን 1992 ዓ.ም. ክለሳ ተደርጎበታል፣ ኖቬምበር 4 ቀን 1996 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ጁላይ 20 ቀን 1998 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 24 ቀን 1999 ዓ.ም. የጽ/ቤት ሃላፊነቶች ለውጥ ተደርጎባቸዋል፣ ጁን 1 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ፌብሩወሪ 28 ቀን 2006 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ኦክቶበር 18 ቀን 2013 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 5 ቀን 2014 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ሴፕቴምበር 5 ቀን 2018 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ዲሴምበር 17 ቀን 2018 ዓ.ም. ተሻሽሏል፣ ኦገስት 31 ቀን 2021 ተሻሽሏል።